# የልጆች/ህጻናት የቁጠባ ደብተር ሊንቀሳቀስ የሚችልበት

በአዋጅ ቁጥር 985/2009 ንዕስ አንቀጽ 10 መሰረት ጎጎ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበር የተቋቋመው በህብረተሰቡ ዘንድ ያልውን የኢኮኖሚ ችግር ለመቅረፍ ሲሆን ይህንንም የሚያሳካበት የገንዘብ ቁጠባና ግንዛቤ በመፍጠር ነው።

እንደ ሀገራችን የገንዘብ ቁጠባን እንደ ባህል ተጠቅሞ ድህነትን ድል የማድረግ ነገር እንድ መፈክር ከመነገር ውጪ ብዙም ሥራ ያልተሰራበት መሆኑን የምንረዳ ቢሆንም ጎጎ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የኅ/ሥራ ማኅበር የልጆች/ህጻናት ቁጠባን በማስፋፋት እና በማሳደግ ለልጆች/ህጻናት ችግር ጥሎ ከማለፍ ይልቅ ጥሪት ገንዘብ በማኖር የልጆች/ህጻናት ነገ ተስፋቸውን እውን እንዲያደርጉ ጎጎ በልብ ሙሉነት እድሉን ለልጆች ሲያመቻች ታላቅ ደስታ በልጆች እንደሚፈጥር ያውቃል።

## የልጆች/ህጻናት የተቆጠበ ገንዘብ የሚንቀሳቀሰው

1. ልጁ/ህጻኑ እድሜው ከ19 አመት በላይ ሲሆነው በእራሱ ሊንቀሳቀስ ይችላል
2. ልጁ/ህጻኑ በጠና ታሞ ወላጅ/ሞግዚት/ህጋዊ አሳዳጊ ማሳከሚያ ሲያጣ የህክምና ማስረጃ ሲቀርብ።
3. ወላጅ/ሞግዚት/ህጋዊ በጠና ታመው/የአልጋ ቁራኛ ከሆኑ፣ ልጁ/ህጻኑ የትምህርት ቤት ክፍያ የተቸገረ ይሆን እንደሆን ለልጁ/ህጻኑ ከቆጠበው 50% (ሀምሳ ፐርሰንት) ያለወለድ ውጪ ተደርጎ ለወላጅ/አሳዳጊ/በህግ ለተፈቀደለት ወላጅ/ሞግዚት/ህጋዊ ይሰጣል።
4. ወላጅ/ሞግዚት/ህጋዊ ልጁን/ህጻኑን ወደሌላ ሀገር የሚልኩ ከሆነ የሚላክበትን ሀገር የሚያሳይ ከኢንባሲ ህጋዊ ማስረጃ ሲቀርብ።
5. ልጁ/ህጻኑ ወላጅ/ሞግዚቱን/አሳዳጊውን በሞት አጥቶ ልጁን/ህጻኑን የሚረከበው አካል የሚያሳድግበት ያጣ መሆኑ ሲረጋገጥ።
6. ልጁ/ህጻኑ ከዚህ አለም በምት ሲለዩ በወራሽነት ቦታ ላይ ስማቸው ለሰፈረ ሰው በውር መልክ ይተላለፋል።
7. እኝህ ከላይ ከተዘረዘሩት ውጪ ለግል ጉዳይ ለምሳሌ ለቤት አስቤዛ፣ ለልብስ፣ ለጫማ፣ ለትራንስፖርት፣ ለመዝናኛ.... ለመሳሰሉት ጉዳዮች ከልጁ/ህጻኑ ቁጠባ ደብተር ውጪ ማድርግ አይቻልም።